# የሸሪዓ ሕግ፤ ምንነቱ፣ መገለጫዎቹ እና ምንጮቹ

*አልዩ አባተ ይማም*[*]

## አህጽሮተ-ጥናት

*ሸሪዓ በኢስላም የሃይማኖት ማዕቀፍ ውስጥ የሚገኝ መለኮታዊ የሕግ ሥርዓት ነው። ሸሪዓ ሲባል ሁለት የተለያዩ ነገር ግን ቀጥተኛ ዝምድና ያላቸው የሕግ ክፍሎችን ሊወክል ይችላል። አንደኛው ክፍል ለዝርዝር የሸሪዓ ድንጋጌዎች አተረጓጎም እና አዳዲስ ሕግጋትን ለመቅረጽ መንደርደሪያ የሆኑ ጥቅል የሕግ ዓላማዎችን (መቃሲድ)፣ መርሆዎችንና ንድፈ-ሐሳቦችን የሚመለከት ሲሆን፣ እነዚህን መሠረተ-ሐሳቦች በመለኮታዊ ምንጮች በማስደገፍ የሚያጠና ‹የሸሪዓ ሕግ መሠረተ-ሐሳቦች (ኡሱል አል-ፊቅሕ)› የተሰኘ ጥንታዊና ሰፊ የጥናት መስክ ይገኛል። ሁለተኛው ክፍል፣ በቀዳሚ የሸሪዓ ምንጮች ውስጥም ሆነ በኡሱል አል-ፊቅሕ አማካይነት የተደነገጉ፣ ዘርፈ-ብዙ ግለሰባዊና ማሕበራዊ ግንኙነቶችን የሚገዙ ዝርዝር ሕጎችን (ፊቅሕ) የሚመለከት ነው። የሸሪዓ ሕግ ቁርአን፣ ሱናሕ እና አመክንዮአዊ የሕግ ምርምር (ኢጅቲሓድ) የተሰኙ ሦስት ምንጮች ያሉት ሲሆን፣ በእነዚህ ምንጮች ላይ ተመርኩዞ የተዘረጋው የሕግ ማዕቀፍ አምልኳዊ (ዒባዳት) እና ዓለማዊ (ሙዓመላት) በሚል ሁለት ምድቦች ተከፍሎ ይታያል፡ ፡ ዓለማዊ የሸሪዓ ሕጎች፣ የግለሰብና የማሕበረሰብ ጥቅም የማስከበር፣ ሰላምና ደህንነትን የማረጋገጥ፣ ጉዳትና እንግልትን የመቀነስና የማስወገድ ዓላማ ያነገቡ ናቸው። የሸሪዓ ሕግ በባህርይው የሕብረተሰቡን የሁኔታዎች ለውጥ ተከትሎ ሊሻሻልና ሊለወጥ የሚችልበት የአመክንዮአዊነት፣ የተለማጭነት፣ የነባራዊነት ባህርያት ያሉት የሕግ ማዕቀፍ ነው።*

**ቁልፍ ቃላት**: ሸሪዓ፣ *ፊቅሕ*፣ የሸሪዓ ምንጮች፣ ቁርአን፣ *ሱናሕ፣ ኢጅቲሓድ*፣ ተለማጭነት፣ አመክንዮአዊነት

## መግቢያ

ኢትዮጵያ የልዩ ልዩ ብሔረሰቦችና ባህሎች መገኛ የመሆኗን ያህል የሐይማኖት ብዝኃነትም የሚንጸባረቅባት ሃገር ናት። የሕግ ሥርዓቱም ሲቀረጽ የሃይማኖት ብዝኃነቱን ተከትሎ ሊመጣ የሚችለውን ማሕበረሰባዊ ጥያቄ በሚመልስ አኳኋን ነው። በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 27 መሠረት ማንኛውም ሰው ሐይማኖቱን በግልም ሆነ በቡድን የመስበክ እና የመተግበር መብት እንዳለው ያረጋግጣል። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የፌዴራል ሥርዓተ-መንግሥት በሰፈነባቸው ሃገራት ውስጥ ሐይማኖትን በግልም ሆነ በሕብረት እንዲሁም በተቋማዊ ቅርጽ የማራመድ መብት ካለው የብዝኃነት እውነታ እና ዓለማዊ አስተዳደር (Secular Governance) ጋር ተጣጥሞ የሚተገበርበትን ሁኔታ ከንድፈ-ሐሳባዊ የሕገ-መንግሥት ዳሰሳዎች ጀምሮ፣ የሰብዓዊ መብቱን ትንታኔ እንዲሁም ዓለም-አቀፍ ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ ከሃገራችን እውነታ አኳያ ጥናት ሊደረግበት የሚገባ

[*] (LL.B, LL.M, PhD Student, School of Law, Bahir Dar University) Email: alyuabate09@gmail.com

ርዕሰ-ጉዳይ እንደሆነ እየጠቆምኩ፣ የዚህ ጥናት ዓላማ የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት በፈቀደው ወሰን ውስጥ በመሆን የሸሪዓ ሕግ፣ የሕግ ሥርዓቱ አካል በሆነው መጠን ሸሪዓዊ ፍትሕን ለሙስሊሙ ማህበረሰብ እንዲያደርሱ በተቋቋሙ የፌዴራልና የክልል የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እና ለሰፊው የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ የሸሪዓን ምንነትና ባህርያት፣ በምንጮቹና መሠረታዊ የሕግ መርሆዎቹ ላይ ግንዛቤ መፍጠር ነው።

## 1. የሸሪዓ ሕግ ምንነት

### 1.1. ሸሪዓ እና *ፊቅሕ*

በ*ኡሱል አል-ፊቅሕ* እና በ*ፊቅሕ* ጥናት ውስጥ ‹ሸሪዓ› እና *‹ፊቅሕ›* የተሰኙት ቃላት የኢስላምን የሕግ ክፍል ለማመላከት አንዱ ሌላውን እየተካ በተለዋዋጭነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ቢሆንም፣ ሙያዊ አገባባቸውን ስንመለከት የተለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። ሸሪዓ ሲባል በመለኮታዊ *ራዕይ (ወሀይ)* የተገለጸውን፣ በቁርአን እና በ*ሱናሕ* ውስጥ የሚገኙትን የሕግ ድንጋጌዎች የሚመለከት ሲሆን፣ *ፊቅሕ* ደግሞ የኢስላምን የሕግ ክፍል የሚያመለክት ቢሆንም በሕግ ሊቃውንት የሕግ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* ያደገውን የሕግ ክፍል የሚወክል ነው። ስለዚህ ሸሪዓ የ*ወሀይ* ውጤት ሲሆን፣ *ፊቅሕ* ደግሞ የምሁራን የምርምር ወይም የሕግ አመክንዮ *(ኢጅቲሓድ)* ውጤት ነው። በተጨማሪም ማንኛውም *ኢጅቲሓድ* መሠረቱና መነሻው ቁርኣናዊ የሕግ ድንጋጌዎች *(አያሕ አል-አህካም/ፊቅሕ አል-ቁርኣን)* ወይም የ*ሀዲስ* የሕግ ድንጋጌዎች *(አሃዲስ አል-አህካም)* ወይም በጥቅሉ መለኮታዊ ምንጭ በመሆኑ *ፊቅሕ* በራሱ የሸሪዓ መሠረቱን የጠበቀ እንደሆነ ይገነዘቧል።[1]

የኢስላም ቀዳሚ ምንጮች በሆኑት ቁርአን እና *ሱናሕ* የተደነገጉት ሕጎች ብዛት በ*ኢጅቲሓድ (ፊቅሕ)* ካደገው አኳያ ሲታይ በጣም ጥቂት ነው። ቁርአን በጠቅላላው ካሉት 6235 አናቅጽ መካከል 350 ያህሉ ብቻ ሕግ-ነክ ድንጋጌዎች ሲሆኑ፣ ቀሪውና ሰፊው የቁርአን ክፍል በእምነት እና በግብረ-ገብነት ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ነው።[2] ስለዚህ ቁርአን እና *ሱናሕ* የሕግ ፍልስፍናዎቹንና *መርሆዎቹን* በመዘርጋት ለሰፊው *የፊቅሕ ማዕቀፍ መሠረት* ቢሆኑም፣ የሰውን የዕለት-ተዕለት እንቅስቃሴ በመግዛት ረገድ በማይነፃፀር ደረጃ መጠነ-ሰፊ የኢስላም ድንጋጌዎች የተዘረጉት በ*ወሀይ* (ሸሪዓ) አማካይነት ሳይሆን በ*ፊቅሕ (ኢጅቲሓድ)* የሕግ ምርምር አማካይነት ነው።[3]

የሸሪዓ እና *የፊቅሕ ድንጋጌዎች*፣ ለ*ኢጅቲሓድ* ካላቸው ተገዥነት አንጻር፣ በሁለት ምድቦች ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ፤ አምልኳዊ የሸሪዓ ሕግጋት *(ዒባዳት)* አንደኛውን ክፍል የሚይዝ ሲሆን፣ በዚህ ምድብ *ሥር* የሚመደቡት ሕግጋት ከዕለት ተዕለት የሰው እንቅስቃሴ ጋር ያልተያያዙ፣ የአምላክ ታዛዥነትን እና ተገዥነትን ለማሳየት የሚፈጸሙ የአምልኮ *ሥ*ርዓቶች ናቸው። ሁለተኛው ምድብ፣ ከሰው የርስበርስ ግንኙነትን ለመግዛት የተደነገጉ የሸሪዓ እና *የፊቅሕ ሕግጋቶች (ሙዓመላት)* ናቸው። የአምልኮ ሕግጋት ትንታኔዎች ዐቢይ በሚባሉት በ*ሶላሕ* (*ሥ*ግደት)፣ *ዘካሕ* (አስገዳጅ ምጽዋት)፣ በ*ሀጅ* ወዘተ. የአምልኮ ተግባራት

[1] Mohammad Hashim Kamali, Source, Nature and Objectives of Shariah, *Islamic Quarterly*, Vol. 33 (1989), p. 216.
[2] Ibid.
[3] Ibid.

ርዕስ ስር የሚብራሩ ሲሆን፣ በእነዚህ ርዕሰ-ጉዳች ላይ የሚደረገው የሕግ ትንታኔ እምብዛም ልዩነት አይንጸባረቅበትም፡፡[4] ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ አምልኳዊ ሕጎች በ*ኑሱስ* (ግልጽ የቁርአንና የሱናሕ ድንጋጌዎች) እንደተገለጹ በቀጥታ ተግባራዊ የሚደረጉ በመሆኑ ነው፡፡ *የሙዓመላት* ሕጎች በአንፃሩ ለመጠነ-ሰፊ *ኢጅቲሓድ* በራቸው ክፍት የሆነ እና የኢስላም ሕግ ተለዋዋጭነት እና ነባራዊነት ባህርይ የሚንጸባረቅባቸው የሕግ ዓይነቶች ናቸው፡፡

## 1.2. አቢይ ርዕሰ-ጉዳዮች እና አመዳደቦች

የኢስላም ሕግ በቀዳሚ ምንጮች ውስጥ እንደተደነገገው (ሸሪዓ) ወይም በሊቃውንት ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* እንደተለየው *(ፊቅሕ - The Corpus Juris of Islamic La*w) በሁለት ምድቦች ተከፍሎ ይታያል፡፡ ይህ የሁለትዮሽ የኢስላም ሕግ አመዳደብ በአራቱም የሱኒ የሕግ ትምህርት ቤቶች *(መዛሒብ)*[5] እና በሸሪዓ የሕግ ክፍሎች ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ችሏል፡፡ *ዒባዳትን* (አምልኮዎችን) የሚመለከቱ ሕግጋት አንደኛውን ምድብ የሚይዙ ሲሆን፣ እነዚህ ሕጎች ሰው ለፈጣሪው ሲል (ለራሱ ሲል) የሚፈጽማቸው አምልኳዊ ክንውኖችን የሚገዙና *ሥነ-ሥርዓቶችን* የሚዘረጉ ናቸው፡፡[6] በሁለተኛው ምድብ ስር የሚመደቡት ደግሞ ዓለማዊ የሕይወት እንቅስቃሴዎችን እና ግንኙነቶችን *(ሙዓመላት)* የሚገዙ ሕጎች ሲሆኑ፣ የእነዚህ ሕግጋት ዓላማ ለሰው ጠቀሜታን ማስገኘት ወይም ጉዳትን ማስወገድ *(መስላሃሕ)* ነው፡፡[7]

*የዒባዳሕ* ሕጎች በመርሕ ደረጃ በምርምር ሊተነተኑና ተጨማሪ *ሥርዓቶች* ሊታከልባቸው አይችሉም፣ ምክንያቱም ሕጎቹ የተደነገጉበት ምክንያትና ዓላማ በአመክንዮኣዊ ምርምር በርግጥ ሊደረስበት የማይችል በመሆኑ፣ እና በአምልኳዊ ክንውኖች ሂደት ውስጥ ምላሽ ሊያገኙ የሚገቡ፣ በሰው ዓለማዊ ሕይወት ውስጥ ችግርን ሊጋርጡ የሚችሉ ጭብጦች ሊፈጠሩበት የማይችል በመሆኑ ነው፡፡ *የዒባዳት* ሕግጋት ጥቅል የድንጋጌ ምክንያታቸው *(ዒለል)* አንድ ግለሰብ ለፈጣሪው ያለውን ታዛዥነትና ተገዥነት መለካት በመሆኑ፣ ከእያንዳንዱ የአምልኮ ሕግ ጀርባ ያለውን ምክንያት *(ዒላሕ)* በመመርመር ለሌላ አመክንዮአዊ የሕግ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* መነሻ ለማድረግ የሚቻልበትን ዕድል ማግኘት አይቻልም፤ ስለሆነም አምልኳዊ ሕጎች *በኑሱስ* (ግልጽ የቁርአንና የሱናሕ ድንጋጌዎች) እንደተገለጹ በቀጥታ ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናሉ፡፡[8]

*የሙዓመላት* ሕግጋት ደግሞ ከማህበረሰቡ ወቅታዊ ተጨባጭ ችግሮች አኳያ መፍትሔ የማይሰጡ ወይም ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ የማይሰጡ ሆነው ከተገኙ፣ በ*ኢጅቲሓድ* አማካይነት አዲስ ድንጋጌዎች ሊታከልባቸው፣ ወይም ራሳቸው ሊሻሻሉ ወይም ሊቀየሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ *የዒባዳት* ሕግጋት *ኢጅቲሓድ* የማይተገበርባቸው ሲሆን፣ *የሙዓመላት*

---

[4] Mohammad Hashim Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, Oneworld Publications (2008), p. 43.

[5] በሱኒ ሙስሊም ውስጥ ካሉ *የፊቅሕ* ት/ቤቶች ትምህርት ቤቶች መካከል አራቱ ማለትም ሀነፊ፣ ሻፊዒ፣ ማሊኪ እና ሀንበሊ ቀዳሚውን ስፍራ ይዘዋል፡፡ በሺዓ ሙስሊም ውስጥም እንዲሁ፣ ልዩ ልዩ የሕግ እሳቤ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ በሸሪዓ ታሪካዊ አነሳስ እና በሸሪዓ ትምህርት ቤቶች እድገት ላይ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ለመያዝ፣ አልዩ አባተ፣ የሸሪዓ እድገትና ቀዳሚ የሕግ ትምሕርት ቤቶች፡ ከኢትየጵያዊ ምልከታዎች ጋር፣ *Haramaya University Law Review* 8 (2019) ያንብቡ፡፡

[6] Kamali, Source, Nature and Objectives of Shariah, *Supra note* 1.

[7] Ibid.

[8] Ibid.

ሕግጋት ደግሞ ለኢጅቲሓድ ተገዥና ክፍት ናቸው።[9] በሁለቱ የኢስላም የሕግ ክፍሎች መካከል ያለው ልዩነት ባህርያዊ ብቻ ሳይሆን፣ ተጨባጭ የሆነ ሕግ ውጤት ልዩነትም አላቸው። ይኸውም፣ የአምልኮ ሕግጋት በፍትሕ ተቋማት አማካይነት አፈጻጸም ሊያገኙ የማይችሉና ዳኝነት ሊጠየቅባቸው የማይችሉ *(Non-justiciable)* መሆናቸው ነው። *ዒባዳት* የአምላክንና የግለሰብን ቀጥተኛ ተዋረዳዊ ግንኙነት የሚመለከቱ እና በተጓዳኝ ያለ የግለሰቦች ወይም የሕዝብ ጥቅም ጣልቃ ሊገባበት የሚችልበት እድል የሌለ በመሆኑ፣ በፍርድ ቤት ወይም በመንግሥት የፍትሕ አስተዳደር ሥርዓት አማካይነት ተፈጻሚ ሊደረጉ አይችሉም። የ*ሙዓመላት* ሕጎች ደግሞ መነሻ ዓላማቸውም ሆነ ጥሰት ቢፈጸም የሰውን ምድራዊ ሕይወት በቀጥታ የሚዳስሱ በመሆናቸው በፍርድ ቤት ሊዳኙ የሚችሉ *(Justiciable)* ናቸው።[10]

የ*ዒባዳሕ* ሕግጋት እንደገና በአምስት ንዑስ ክፍሎች ሥር ይተነተናሉ፤ እነዚህም ንጽህና *(ጦሓራሕ)*፣ *ሶላህ* (*ሥግደት*)፣ *ጾም*፣ የሐጅ ጉብኝት እና አስገዳጅ ምጽዋት *(ዘካሕ)* ናቸው። ሁሉም *የፊቅሕ* ድርሳናት ማለት ይቻላል በ*ዒባዳሕ* የሕግ ማብራሪያዎች የሚጀምሩና የሕግ ትንታኔዎቻቸው በእነዚህ አምስት አቢይ የ*ዒባዳት* ርዕሶች ሥር ተደራጅተው የቀረቡ ናቸው።[11]

የሀነፊ የሕግ ትምህርት ቤት ሊቅ የሆኑት ኢብን ዐቢዲን አጠቃለው እንዳስቀመጡት፣ ኢስላም ማለት፣ የቀኖናዎች (የእምነት ማዕዘናት - *ኢዕቲቃዳት*)፣ የ*ሥነ-ምግባር* እሴቶች (*አዳብ*)፣ አምልኳዊ ተግባራት *(ዒባዳት)*፣ ግለሰባዊ ግንኙነቶች *(ሙዓመላት)* እና የወንጀል ሕጎች *(ዑቁባት)* ድምር ሥርዓት ነው።[12] የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ በሕግ ክፍል ሥር ሳይሆን በእምነት *(ዓቂዳሕ)* ሥር የሚመደቡ ሲሆኑ *ዒባዳት* (አምልኮዎች) በምግባር የሚከወኑ እና ራሳቸውን ችለው መቆም የሚችሉ የአመለካከት ወይም የእምነት እሳቤዎች ባለመሆናቸው፣ *የፊቅሕ* አካል መሆናቸው አግባብነት አለው። ቀሪዎቹ ሁለቱ፣ ማለትም *ሙዓመላት* (ግለሰባዊ) እና *ዑቁባት* (ወንጀል) ጉዳዮች የሕግ አጀንዳዎች መሆናቸው ግልጽ ነው። በ*ኢዕቲቃዳት*፣ *አዳብ* እና *ፊቅሕ (ዒባዳት* እና *ሙዓመላት)* መካከል ያለው ልዩነት፣ ጉዳዮች ለዳኝነት ቀርበው ሕጋዊ መፍትሔ ሊሰጣቸው ከመቻላቸው አኳያ *(Functional Approach)* ታይተው መሆኑን ይገነዘቧል፤ አለበለዚያ አንድን ሰው አምልኳዊ ተግባራትን እንዲፈጽም የሚያደርገው በቅድሚያ የያዘው የእምነት ቀኖና ነው፤ እንዲሁም አምልኳዊ ክንውኖች በፈጣሪ ዘንድ ጽኑእነት ይኖራቸው ዘንድ በትክክለኛ የእምነት ጽንሰ-ሐሳብ ላይ የተገነቡ መሆን ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም፣ ከላይ የተገለጹት ምድቦች የአንድ የሃይማኖት ማዕቀፍ አካል በመሆናቸው፣ እርስበርሳቸው የጠበቀ ትስስር እንዳላቸው ሊዘነጋ አይገባም።

የ*ሙዓመላት* ሕጎች ከ*ዒባዳት* የሚለዩት፣ የአምልኮ ተግባራትን በመከወን የሚገኘውን መለኮታዊ ምንዳ የ*ሙዓመላት* ሕግጋትን በመተግበር የማይገኝ በመሆኑ ሳይሆን፣ ሕጎቹ እስከተፈጸሙ ድረስ ለተግባሩ መነሻ የሆነው አሳብ *(ኒያሕ)* ለዳኝነት አወሳሰን ታሳቢ የማይደረግ መሆኑ ነው። ስለሆነም ሙስሊም (አማኝ) ያልሆነ ሰው ቢሆን እንኳ

---

[9] Ibid.

[10] Ibid, p. 217.

[11] Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, *supra* note 4, pp. 43-44.

[12] Ibid, p. 44.

*ሙዓመላት* ሕጎችን እስከተገበረ ድረስ፣ በሸሪዓ ፍርድ ቤት እይታ ሕጉ እንደተፈጸመ የሚቆጠር ይሆናል።[13] ዓለማዊ ሕጎች በትክክለኛው እሳቤ-መለኮት *(ኒያሕ)* ወይም ለፈጣሪ ታዛዥ ለመሆን በሚል የተፈጸሙ ከሆነ በፍርድ ቤት አይን ሕጉ እንደተፈጸመ ከመቆጠሩ በላይ እንደ አምልኳዊ ተግባራት ሁሉ መንፈሳዊ ፋይዳ ማስገኘት ይችላሉ። ባጭሩ በመንፈሳዊ (የእምነት) እና በሕግ መካከል ልዩነት ሲፈጠር፣ ከጽንሰ-ሐሳባዊ ትንታኔው አኳያ፣ እና ከዳኝነት እና ከአፈጻጸም አንፃር ካለው ልዩነት በመነሳት እንጂ በመካከላቸው ሊኖረው የሚችለው አሳባዊ (*ሥነ-አዕምሯዊ*) እና መለኮታዊ ትስስር እንደተጠበቀ መሆኑን ይገነዘቧል።

## 2. የሸሪዓ ምንጮች

የሸሪዓ ምንጮች በመለኮታዊ ራዕይ የተገለጹ *(Revealed)* እና አመክንዮኣዊ *(Rational)* ተብለው በሁለት ምድብ ሊከፈሉ ይችላሉ። የራዕይ ምንጮች የሚባሉት ቅዱስ ቁርአን እና *ሱናሕ* ናቸው። አመክንዮአዊ ምንጮች ወይም አስረጂዎች በቁጥራቸው ብዙ ሲሆኑ በሰው አዕምሯዊ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* ላይ የተመሠረቱ ናቸው፤ ስለሆነም ሦስተኛው የሸሪዓ ምንጭ በጠቅላይ ቃል *ኢጅቲሓድ* ነው ማለት ይቻላል።[14] *ኢጅቲሓድ* የተለያየ ቅርጽ እና በተለያዩ የሕግ ንድፈ-ሐሳቦች ላይ ሊመሰረት ይችላል። ለምሳሌ፣ በ*ቂያስ* (ምስስሎኣዊ/analogy/ *አመክንዮ*)፣ *ኢስቲህሳን* (ርትዕ)፣ *ኢስቲስሃብ* (የቀጣይነት ግምት) ወዘተ. ይገኙበታል።[15] *ኢጅቲሓድ* ግለሰባዊ ወይም ቡድናዊ (የወል) ቅርጽ ሊይዝ ይችላል። የሕግ ምርምሩ የተደረገው በአንድ ብቁ በሆነ የሸሪዓ ሊቅ *(ሙጅተሒድ)* ከሆነ ግለሰባዊ *ኢጅቲሓድ* ሲሆን፣ በብዙኃን ሊቃውንት የተንጸባረቀ፣ የቀድሞ ወይም ዘመነኛ፣ አቋም ሲሆን ደግሞ *ኢጅማዕ* ይባላል።[16]

### 2.1. ቁርኣን

ቁርአን በቀዳሚ ምንጭነቱ በውስጡ የያዛቸው የሕግ ድንጋጌዎች በጣም ጥቂት እንደመሆናቸው እንደ ሕግ ሰነድ ሊወሰድ አይችልም። ቁርአን እንደ ሕግ መጽሃፍ ሳይሆን ራሱን ተግሳጽ *(ዚክር)*፣ *መመሪያ (ሁዳ)* በተሰኙ *ሥያሜዎች* ይጠራል። *ኢያት አል-አህካም* የሚባሉት የቁርአን የሕግ ድንጋጌዎች፣ ከአጠቃላይ 6235 አናቅጽ መካከል ወደ 350 የሚሆኑትን ብቻ ይይዛሉ። እነዚህ ቁርአናዊ ሕጎች ለሰፊው የ*ኢጅቲሓድ* ድርሳን መንደርደሪያ በመሆን የቁርአኑን የሕግ ፍልስፍና ይመሠርታሉ።[17]

ከ350 የሕግ አንቀጾች መካከል 140 የሚሆኑት እንደ *ሶላሕ፣ ሀጅ፣ ዘካሕ* እና *ሰደቃሕ፣* መሐላ ለመሳሰሉ አምልኳዊ ተግባራት የአፈጻጸም *ሥነ-ሥርዓቶችን* የሚደነግጉ ናቸው። ወደ 70 የሚሆኑ አንቀፆች ደግሞ ጋብቻን፣ ፍቺን፣ አባትነትን፣ የልጅ አያያዝን፣ ቀለብን፣ ውርስን እና ኑዛዜን የሚመለከቱ የቤተሰብ ድንጋጌዎች ናቸው። ወደ 30 የሚሆኑ አንቀፆች ደግሞ የወንጀል ድርጊቶችን እና ቅጣቶችን የሚደነግጉ ናቸዉ። 10 የሚሆኑ አንቀፆች

[13] Ibid, pp. 47-48.
[14] Kamali, Source, Nature and Objectives of Shariah, *supra* note 1, p. 219.
[15] Ibid.
[16] Ibid.
[17] አልዩ አባተ ይማም፣ ቀዳሚው የሸሪዓ ሕግ ምንጭ - ቁርኣን፣ *Hawassa University Journal of Law*, Volume 2, (July 2018), ገጽ 133።

ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮዎችን፣ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ናቸዉ፡፡[18] በቁርአን ውስጥ በሚገኙ *አያት አል-አህካም* ብዛትም ሆነ የጉዳዮችን ዓይነት መሠረት በማድረግ የተቀመጠው አኃዝ ላይ የምሁራን ልዩነት ያለ ሲሆን፣ ልዩነቱ ሊፈጠር የቻለው ጥቂቶቹ የሕግ አንድምታ አለው ብለው የተስማሙበት አንድ የቁርኣን አንቀጽ ላይ ሌሎች ደግሞ የሕግ አስረጂነት የለውም በሚል ሳይቀበሉት ይቀራሉ፤ አንዳንዶቹ ከቁርአናዊ ታሪኮች እና ዘይቤያዊ አገላለጾች ላይ ሳይቀር የሕግ ብያኔዎችን ይቀስማሉ፡፡[19] ያም ሆኖ ቁርኣናዊ የሸሪዓ ድንጋጌዎች ቁጥራቸው ከላይ ከተጠቀሰው እምብዛም የማይርቅ መሆኑን ይገነዘቧል፡፡

ቁርኣናዊ *የፊቅሕ* ሕግጋት በአብዛሀኛው ልዩና ዝርዝር ከመሆን ይልቅ ጥቅል እና የመርሆነት ባህርይ ያላቸው ናቸው፤ ይህ ባህርያቸው ዘርፈ-ብዙውን የሰው የዕለት-ተዕለት እንቅስቃሴ እና መስተጋብር ለመቆጣጠር እና በ*ኢጅቲሓድ* አማካይነት ገዥ ሕግጋትን ለመዘርጋት የንድፈ-ሐሳብ መሠረት ይጥላል፡፡[20] ከቁርአናዊ ጥቅል *የፊቅሕ* መርሆዎች ላይ በመመርኮዝ ሌሎች *የኢጅቲሓድ* መርሆዎችን በመለየት፣ ከእነዚህ መርሆዎች ላይ ሌሎች ዝርዝር እና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን ለማውጣት አመቺ ሆኗል፡፡ ይህም የቁርአኑን የሕግ ፍልስፍና ምጡቅነትና እና በዘመን የማይወሰን ገዥነቱን ያረጋገጠ የሕግ ሥልጣኔ መገለጫ ነው፡፡ የልዩ ድንጋጌዎቹ ዓላማ፣ ለጥቅል የሕግ መርሆዎቹ የአተረጓጎም ማሳያ በመሆን በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው፡፡ ቁርአን የመጀመሪያው የሸሪዓ ምንጭ እንደመሆኑ፣ በሁሉም የሕግ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ጠቅላላ መርሆዎችንና መሪ ሕጎችን አካትቷል፡፡ እነዚህ ጥቅል መርሆዎች ደግሞ፣ ሙሉ በሙሉም ባይሆን በ*ሱናሕ* ተብራርተዋል፤ ከዚህ ውጪ ያለው ለ*ኢጅቲሓድ* ምሁራዊ ጥረት የተተወ ነው፡፡[21]

በተጨማሪም የቁርኣን ሕግጋት ልዩ ከመሆናቸው እና ካላቸው ግልጽነት አንፃር *ቀጥዒ* (ወሳኝ/ግልጽ- *Definitive)* እና *ዞኒ* (አሻሚ - *Speculative*) ተብለው በሁለት ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ *ቀጥዒ* የቁርአን ድንጋጌዎች ልዩ እና የተብራሩ በመሆናቸው ትርጉም አያስፈልጋቸውም፤ ስለሆነም ለ*ኢጅቲሓድ* ክፍት አይደሉም፡፡ *ዞኒ* የቁርአን ድንጋጌዎች ደግሞ ብዙውን የቁርአን የሕግ አንቀጾች የሚይዙ፣ እና ከቋንቋቸውም ሆነ ከሚያነሱት ሐሳብ አንፃር ግልጽ ባለመሆናቸው ለትርጉም ክፍት ናቸው፡፡ እነዚህ *ዞኒ* የቁርአን አንቀፆች ለሰፊው *የኢጅቲሓድ* እንቅስቃሴ መነሻ ማዕቀፍ በመሆን ያገለግላሉ፡፡[22]

## 2.2. ሱናሕ

*ሱናሕ* ከቁርአን በመቀጠል በሁለተኛ ደረጃ የሚገኝ ኢስላማዊ የእምነትና የሕግ ምንጭ የሆነውን ነቢያዊ ፈለግ አርዓያነት የሚወክል ነው፡፡[23] ስለሆነም *ሱናሕ* በይዘቱ አስገዳጅ *(ዋጅብ/ፈርድ)* ወይም ፍቁድነትን ወይም ሌሎች የሸሪዓ ድንጋጌ ቅርጾችን *(ሁክም አሽ-ሸርዒ)* ሊይዝ ይችላል፡፡ በ*ሥነ-ቃላዊ* ዘገባ *(ሀዲስ)* አማካይነት ከነቢዩ ሙሀመድ ወደ ባልደረቦች

[18] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 134፡፡
[19] ዝኒ ከማሁ፡፡
[20] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 145-146፡፡
[21] Mohammad Hashim Kamali, *Principles of Islamic Jurisprudence*, The Islamic Texts Society (1991), p, 32.
[22] Kamali, Source, Nature and Objectives of Shariah, *supra* note 1, p. 221.
[23] አልዩ አባተ ይማም፣ *ሱናሕ፦ ሁለተኛው የሸሪዓ ሕግ ምንጭ*፣ *Hawassa University Journal of Law,* (2018), Vol. 2, ገጽ 151.

*(ሶሃቢዩን)* እና የዘመኑ ማህበረሰብ፣ ከዚያም ወደ ተከታይ ትውልዶች በቃል እንዲሁም በመጠኑም ቢሆንም በጽሑፍ ተላልፎ ወደ እኛ የደረሱ ነቢያዊ ንግግሮችን፣ ተግባራትን፣ ተቆጥቦዎችን፣ እንዲሁም ግላዊ ዝንባሌዎችንና ምርጫዎችን የሚይዝ ነቢያዊ ፈለግ ነው። [24]

*ሱናሕ (ሀዲስ)* የሸሪዓ ምንጭ በመሆኑ ላይ፣ እና ክልክል እና የተፈቀደ *(ሀላል እና ሀራም)* የማድረግ አቅሙ ከቁርአን ጋር የሚስተካከል እንደሆነ *ዑለማጰ* በአንድ ድምጽ ይስማማሉ። ለዚህም ተጠቃሹ ምክንያት በነቢዩ *ሙሀመድ* በኩል የሚተላለፉ ትዕዛዞችና ክልከላዎች ምንጫቸው ከአምላክ በመሆኑና፣ ለነቢዩ ትዕዛዝ ተገዥ መሆኑ ለአምላክ መታዘዝ ማለት እንደሆነ በራሱ በቁርአን ውስጥ በተደጋጋሚ የተገለጸ በመሆኑ ነው።[25] አል-ገዛሊ እንዳብራሩት ለነቢዩ *ሙሀመድ* የሚደርሷቸው አምላካዊ *ራዕዮች* ከፊሉ የቁርአን፣ ከፊሉ ደግሞ የ*ሱናሕ* ቅርጽ ይይዛሉ። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ቁርአን ቃል በቃል ከአምላክ የወረደ ፍጹም የፈጣሪ ቃል *(ወህይ ዟሒር)* ሲሆን፣ *ሱናሕ* ደግሞ ሐሳቡ በመለኮታዊ *ራዕይ* ለነቢዩ የተገለጸ፣ በቋንቋዊ አገላለጹ ደግሞ የነቢዩ *ሙሀመድ* እንደሆነ *(ወህይ ባጢን)* ብዙኃን ምሁራን ይስማማሉ።[26] ቁርአን ከአምላክ እንደወረደ ቃል በቃል በጽሁፍ የሰፈረ እና የተረጋገጠ እንደሆነ የሚታመን በመሆኑ፣ እና እስካለንበት ትውልድ ድረስም ቢሆን በይዘቱ ላይ ምንም አይነት ውሃ የሚያነሳ ጥርጣሬ ሳይነሳበት ተጠብቆ የደረሰ በመሆኑ ቁርአንን በተመለከተ የተዓማኒነት ምዘና ማዕቀፍ ማዳበር አስፈላጊ አልነበረም።[27] ከነቢዩ ሕልፈት ብዙም ሳይርቅ ከሦስት *ዐሥርተ-ዓመታት* (በ40 *ዓመተ-ሒጅራ)* በኋላ በልዩ ልዩ *ፖለቲካዊ* እና ቡድናዊ የእምነት አቋሞች ምክንያት የሐሰት *ሀዲሶች መፈጠራቸው*፣ እንዲሁም ዋነኛው የ*ሀዲስ* አሰባሰብ እና በጽሁፍ መስፈር የተከናወነው ከ*ሒጅራ* ከአንድ ምዕተ-ዓመት በኋላ በመሆኑ፣ ከነቢዩ ተገኙ የሚባሉ *ሀዲሶች*፣ በይዘታቸው እና በአዘጋገባቸው ላይ የተዓማኒነት ጥያቄዎች እንዲነሳባቸው ምክንያት ሆኗል።[28] በመሆኑም የ*ሀዲስ* ዘገባዎች ተዓማኒ እና በተከታታይ እማኞች የተላለፈ *(ሙተዋቲር)* ሊሆን፣ ወይም ደግሞ በተዓማኒነት ደረጃው አጠራጣሪ *(አሃድ)* ሊሆን ይችላል።[29] በየትኛውም የአዘጋገብ አይነት ቢሆን፣ *ሀዲሶች* የሸሪዓ ምንጭ (አስረጂ) ሆነው የሚቀርቡ መሆናቸው አከራካሪ አይደለም።[30]

*ሱናሕ* እንደ ሸሪዓ ምንጭ፣ የሕግ ድንጋጌዎችን በሦስት ደረጃዎች ሊደነግግ ይችላል። አንደኛ፣ በቁርአን የተገለጹ መርሆዎች እና ልዩ ድንጋጌዎችን በድጋሜ በ*ሀዲስ* ሲገለጹ እና ሲጠናከሩ ነው። በዚህ ሚናው *ሀዲስ* በቁርአን ከተደነገገው ድንጋጌ ላይ የሚጨምረው አዲስ ፍሬ-ሐሳብ ባይኖርም፣ ቁርአናዊ ድንጋጌዎችን በተለየ አነጋገር በመግለጽ ለአረዳድ ቀላል እንዲሆኑና አጽንኦት እንዲያገኙ ያደርጋል። ሁለተኛው የ*ሱናሕ* የምንጭነት ሚና በቁርኣን የተገለጹ መርሆዎችንና ድንጋጌዎችን ወይም ግልጽ ያልሆነውን የቁርአን የሕግ ክፍል

---

[24] ዝኒ ከማሁ

[25] Kamali, Source, Nature and Objectives of Shariah, *supra* note 1, p. 222. ቁርአን፣ 4፡80 እና 59፡7 ይመለከቷል።

[26] Kamali, *Principles of Islamic Jurisprudence*, *supra* note 21, p. 14.

[27] አልዩ፣ *ቀዳሚው የሸሪዓ ሕግ ምንጭ*፣ *ግርጌ ማስታወሻ* 17፣ ገጽ 131-132 ይመለከቷል።

[28] አልዩ፣ *ሱናሕ፦ ሁለተኛው የሸሪዓ ሕግ ምንጭ*፣ *ግርጌ ማስታወሻ 23*፣ ገጽ 161-162።

[29] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 181-185።

[30] Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, *supra* note 4, pp. 23-24.

ግልጽ በማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የቁርአኑን ጥቅል ድንጋጌ *(ዐም)* ልዩ *(ኻስ)* በማድረግ፣ ያልተገደበውን *(ሙጥለቅ)* የተገደበ/የተወሰነ *(ሙቀየድ)* በማድረግ ያብራራሉ፡፡ አብዛሀኛው የ*ሀዲስ* ዘገባ በእነዚህ ሁለት ምድቦች ሥር የሚወድቅ ሲሆን፣ እነዚህ *ሀዲሶች (አሃዲስ)* በአረጋጋጭነትም ሆነ በአብራሪነት ሚናቸው የቁርአን አካል እንደሆኑና ከቁርአን ተነጥለው ሊታዩ እንደማይችሉ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ ሦስተኛው የ*ሀዲስ* ሚና በቁርአን ያልተገለጸን አዲስ ሕግ በ*ሀዲስ* ሲደነገግ ነው፤ የዚህ አይነት ሀዲሶች መሥራች ሀዲሶች *(ሱናሕ አል-ሙአሲሳሕ)* ይባላሉ፤ ከቁርአን ጋር ትስስር ሳይኖራቸው፣ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ የሕግ ምንጮች ይሆናሉ፡፡[31]

## 2.3. ኢጅቲሓድ

በሦስተኛ ደረጃ የሸሪዓ ምንጭ ሆኖ የሚቀመጡት አመክንዮኣዊ አስረጂዎች ወይም በሕብር ስማቸው *ኢጅቲሓድ* ናቸው፡፡[32] *ኢጅቲሓድ* ማለት በልዩ ልዩ ጭብጦች ላይ ሕግጋትን ከምንጮቹ ለመቅሰም፣ በሸሪዓ ሊቅ *(ሙጅተሒድ)* የሚደረግ ምሁራዊ - አመክንዮኣዊ ጥረት ማለት ነው፡፡[33] *ኢጅቲሓድ* በአንድ በኩል ምንጮችን በማጣቀስ፣ በመተርጎም፣ በመተንተን፣ ሕግጋትን መለየት ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሸሪዓውን አቋም መግለጽ *(ፈትዋ)* ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ *ኢጅቲሓድ* ቀዳሚ የሸሪዓ ምንጮችን በመተርጎም ሂደት ለአንድ የሕግ ጥያቄ ብይን ላይ መድረስ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ አይነቱ *ኢጅቲሓድ* እንደ ጭብጥ የተያዘው ጉዳይ መፍትሔ ቀድሞ በቀዳሚ ምንጮች ውስጥ ተለይቶ ወይም በግልጽ ያልተቀመጠ ቢሆንም ለችግሩ ፍንጭ የተመለከተ ሲሆን በዚህ መንደርደሪያ ሐሳብ ላይ በመመርኮዝ የሕግ ትርጉም (ትርጉማዊ *ኢጅቲሓድ)* ለመስጠት ይጋብዛል፡፡ ጭብጡ ከነአካቴው በምንጮች ውስጥ ያልተወሳ ከሆነ፣ ጠቅላላ የሸሪዓ ዓላማዎችን *(መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ)* መሠረት በማድረግ አዲስ ፍርድ *(ሁክም)* ላይ የመድረስ ወይም በሌላ አገላለጽ አዲስ የሸሪዓ ሕግ ለመቅረጽ የሚደረግ አመክንዮኣዊ የምርምር ሂደት ደግሞ ፈጠራዊ *ኢጅቲሓድ* ይባላል፡፡[34]

*ኢጅቲሓድ* የቁርአን እና የሱናሕ የሕግ መርሆዎችና ድንጋጌዎችን ከየወቅቱ እና ከማህበረሰቡ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲዛመድ በማድረግ አግባብነታቸው እና ቀጣይነታቸው የሚረጋገጥበት መሣሪያ ነው፡፡ ሸሪዓ በመርህ ደረጃ ከሁኔታዎች መለዋወጥ ጋር ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል ይችላል፡፡ ይህ የማሻሻያ ወይም የለውጥ ሂደት የሚተገበረው ደግሞ በየክፍለ-ዘመኑ ባሉ የሸሪዓ ሊቃውንት በሚደረግ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* አማካይነት ነው፡፡[35] *ኢጅቲሓድ* የለውጥ እና የቀጣይነት መሣሪያነቱን ያህል በሸሪዓ ሕግ ውስጥ መሻር *(ነስኽ)* እንዳለ በጣት ከሚቆጠሩ ምሁራን በስተቀር ሁሉም የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡[36] የ*ነስኽ* መኖር የሚያስረዳው ዋናው ቁምነገር ደግሞ በአንድ ወቅት ወይም ሁኔታ የወረደ መለኮታዊ ሕግ፣ በነባራዊው ሁኔታ መቀየር ምክንያት ሕጉ ሊቀየር እና በሌላ ሕግ ሊተካ የሚችል መሆኑን ነው፡፡ የሸሪዓ ዓላማ በማይለወጥ እና በማይሻሻል ግትር ሕግ፣ በሰው

---

[31] Kamali, Source, Nature and Objectives of Shariah, *supra* note 1, p. 222.
[32] Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, *supra* note 4, p. 166.
[33] Ibid, pp. 162-163.
[34] Ibid, p. 162.
[35] Ibid, p. 166.
[36] Kamali, *Principles of Islamic Jurisprudence*, *supra* note 1, p. 139.

ምድራዊ ሕይወት ላይ ሥንክሣር ማብዛት ወይም በችግር የተሞላ እንዲሆን ማድረግ ሳይሆን ቀላል እና ምቹ ሕይወት እንዲመራ ማስቻል ነው፤[37] ለዚህም ሲባል በአንድ ወቅት ተገቢ የሆነ መለኮታዊ ሕግ፣ በሌላ ጊዜ አግባብነት ሳይኖረው ስለሚችል ከሰው ሳይሆን ከራሱ ከአምላክ በሆነ የመሻር ተግባር *(ነስኽ)* እንዲለወጥ ተደርጓል፡፡[38] ይህ ከሆነ ታዲያ የሸሪዓ ድንጋጌዎች ለውጥ ወይም ማሻሻያ ሳይደረግባቸው የሚተገበሩ ከሆነ ዓላማቸውን በማያሳካ፣ ብሎም ችግር በሚያባብስበት ሁኔታ ውስጥ፣ በ*ኢጅቲሓድ* አማካይነት እንዲለወጡ የማይደረግበት ወይም የማይሻሻልበት ምክንያት አይኖርም፡፡

የሸሪዓ ሕግ አምልኳዊ ጉዳዮችን *(ዒባዳት)* የሚመለከት ከሆነ ለለውጥ ወይም ለሕግ ማሻሻያ ተገዥ እንዳልሆነ ወጥ የሆነ አቋም አለ፡፡ ምክንያቱም የእነዚህ ድንጋጌዎች ዓላማ ምድራዊ ሕይወትን መምራትና በትክክለኛው ጎዳና ላይ እንዲራመድ ማድረግ ሳይሆን፣ ሰው ለአምላኩ ያለውን ተገዥነት ለመለካት የተደነገጉ በመሆኑ ተጨባጭ እውነታዎችን መሠረት በማድረግ ሊቀየሩ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡[39] የሸሪዓው ድንጋጌ አምልኮን ሳይሆን ዓለማዊ የኑሮ መስተጋብርን የሚመለከት *(ሙዓመላት)* ከሆነ ሕጉ የሕብረተሰቡን ነባራዊ እውነታ የተከተለና እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን ያገናዘበ መሆን ይገባዋል፡፡ ስለሆነም *በሙዓመላት* ላይ ያሉ የሸሪዓ ሕጎች በ*ነስኽ* አማካይነት አንደተለወጡ ሁሉ *በኢጅቲሓድ* አማካይነትም ይቀየራሉ፤ ይሻሻላሉ፡፡ የቁርኣንና የሱናሕ ድንጋጌ ልዩ እና ግልጽ በመሆኑ ምክንያት ለትርጉም ክፍተት የማይሰጥ በሆነ ጊዜ፣ *ኢጅቲሓድ* የማይፈቀድ መሆኑ የብዙኃኑ ምሁራን ስምምነት አለ፡፡ ይህ ቢሆንም ልዩ የቁርአን ድንጋጌዎች ነባራዊ ሁኔታውን በማገናዘብ ለውጥ የተደረገባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ ከነቢዩ ሙሀመድ ሕልፈት በኋላ ከተተኩ የኢስላም አመራሮች ታሪክ እንረዳለን፡፡[40] ባጠቃላይ፣ ቀላል እና ምቹ ምድራዊ ሕይወትን ማረጋገጥ ወይም ‹ችግርን መቅረፍ ወይም ተግዳሮቶችን ማስወገድ *(ረፍዕ አል-ሐረጅ)*› በተሰኘው ቁርኣናዊ መርሆ[41] መሠረት የኢስላም ሊቁ አል-ቀራፊ፣ በጉዳዩ ላይ እንዲህ ሲል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፤ ‹‹የሕብረተሰብ ልማድ እና ነባራዊ እውነታ ተንተርሰው የተደነገጉ የሸሪዓ ሕጎች፣ ልማዱ ወይም ሁኔታው በመለወጡ ምክንያት ሊለወጡ ይገባል፡፡››[42]

*ኢጅቲሓድ* በሸሪዓ ምንጭነቱ በሦስት ደረጃዎች ሊፈጸም ይችላል፤ አንደኛ፣ በመልዕክታቸው *(ደላላሕ)* *ዞኒ* የሆኑ የቁርአን አናቅጽ፣ ወይም በይዘትም ሆነ በዘገባ ሠንሰለታቸው *(ሪዋያሕ)* ምክንያት *ዞኒ* (ግልጽ ያልሆኑ/አጠራጣሪ) የሆኑ የ*ሀዲስ* ዘገባዎች ላይ ከሕግጋቱ ዓላማ ጋር በሚጣጣም መልክ ትርጉማዊ *ኢጂቲሓድ* ይደረጋል፡፡ የዚህ *ኢጅቲሓድ* ዓላማ ግልጽ ያልሆኑ ቀዳሚ የሸሪዓ ድንጋጌዎችን ግልጽ ማድረግ ነው፡፡[43] በሁለት ግልጽ ድንጋጌዎች

[37] ቁርአን፣ አል-ብቀራሕ፣ 2፡185 ይመለከቷል፡፡
[38] ቁርአን፣ አል-ብቀራሕ፣ 2፡106፣ 16፡101 ይመለከቷል፡፡
[39] Kamali, Sharia *Law: An Introduction*, *supra* note 4, p. 26.
[39] Ibid.
[40] Kamali, *Principles of Islamic Jurisprudence*, *supra* note 21, p. 218.
[41] Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, *supra* note 4, p. 26.
[42] Ibid.
[43] Kamali, Source, Nature and Objectives of Shariah, *supra* note 1, p. 224.

መካከል ግጭት ቢኖር፣ የአስረጂዎች መጣረስን *(ተዐሩድ)* በሚገዙ መርሆዎች መሠረት አንዱን መምረጥ የሙጅተሒድ ተግባር ነው።[44]

ሁለተኛ፣ በሸሪዓ ቀዳሚ ምንጮች ምንም ዓይነት አስረጂ በማይገኝላቸው፣ ወይም *ኢጅማዕ* (የምሁራን የጋራ አቋም) በሌላቸው ጉዳዮች ላይ የሚደረገው *ኢጅቲሓድ* መነሻ ፍንጭ የማይገኝለት በመሆኑ፣ በዋናነት መንደርደሪያ በመሆን የሚያገለግሉት የሸሪዓ ጥቅል ዓላማዎች *(መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ)* ናቸው። ይህ አይነቱ *ኢጅቲሓድ ‹ኢጅቲሓድ ቢ ረዕይ›* (በግል አስተያየት ላይ የተመሠረተ *ኢጅቲሓድ*) ይባላል።[45]

ሦስተኛ፣ ቀድመው በ*ፊቅሕ* የተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ያሉ ሕጎች፣ የተደነገጉባቸው መነሻ ከባቢያዊ ሁኔታዎች በመለወጣቸው ምክንያት የሕጎቹ አግባብነት የተቋረጠ ከሆነ እና ሕጎቹን ቃል በቃል እንዲፈጸሙ ማድረግ የሕጎቹን ዓላማዎችና ጠቅላላ የሸሪዓ ግቦችን ማሳካት የማይቻል ከሆነ፣ *ሙጅተሒዱ* ነባራዊ ሁኔታውን እና በተጨባጭ *ያጋጠሙ* ችግሮችን በማገናዘብ አዲስ *ኢጅቲሓድ* በማድረግ፣ የቀደምት ሕጎችን ሊቀይር ወይም ሊያሻሽል ይችላል።[46] የቀድሞው *የፊቅሕ* ድንጋጌ በ*ቂያስ* (ምስስሎኣዊ አመክንዮ)፣ በ*ኢስቲህሳን* (ርትዕ) ወይም በሌሎች የ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎች አማካይነት ድምዳሜ ላይ የተደረሰበት ሊሆን ይችላል፤ አዲሱም *ኢጅቲሓድ* በእነዚህ መርሆዎች ላይ ተመርኩዞ የተለየ የ*ፊቅሕ* ድምዳሜ ላይ ሊደርስ ይችላል። በሁለቱ የ*ኢጅቲሓድ* ምርምሮች መካከል ያለው ልዩነት በተለያየ የማሕበረሰብ ተጨባጭ እውነታዎች ውስጥ የሚከናወኑ መሆናቸው ነው።

## 3. የሸሪዓ መገለጫ ባህርያት

### 3.1. የሸሪዓ ሃይማኖታዊ እና ዓለማዊ ገጽታዎች

ሸሪዓ ዘርፈ-ብዙ አምልኳዊ *ሥነ-ሥርዓቶችን* እና ዓለማዊ ግንኙነቶችን የሚገዙ ሕጎችን አቅፎ የያዘ ሰፊ የሕግ *ሥርዓት* እንደሆነ ቀደም ባሉት ርዕሶች ስር ተገልጿል። ይህ የሁለትዮሽ የሸሪዓ ባህርይ የሕግ *ሥርዓቱን* ሃይማኖታዊ እና ዓለማዊ (ግብረ-ገባዊ) ገጽታ የሚያንጸበርቅ ነው። ፍጹም ሃይማኖታዊነት ወይም መንፈሳዊነት ባህርይ ያላቸው፣ በዓለማዊ ሕይወት ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ የሌላቸው ድንጋጌዎች፣ በመንግሥታዊ የፖለቲካ ማሕበረሰብ አስተዳደር ውስጥ ተፈጻሚ ሊደረጉ አይችሉም:: ምክንያቱም ቅጣት አዘል በሆነ ዓለማዊ የፍትሕ አስተዳደር ተቋማት አማካይነት ተፈጻሚ እንዲሆን ቢደረግ፣ በሕብረተሰባዊ አኗኗር ውስጥ የሚጨምረው እሴት ካለመኖሩም በተጨማሪ፣ የአምላካዊ ሕግን ዓላማ አያሳካም። አምልኳዊ ሕጎች በግለሰብ ደረጃ፣ ከእምነትና ከተገዥነት በመነጨ ስሜት የሚተገበሩ እንጂ በውጫዊ ምክንያቶችና በቅጣት ፍርሐት የሚፈጸሙ ከሆነ፣ የእምነት ነጸብራቅነታቸው የሚወገድ በመሆኑ፣ እና በምትኩም የሚያመጣው ማሕበረሰባዊ

[44] Ibid.
[45] Ibid.
[46] Ibid.

ጥቅም ወይም የሚቀርፈው ችግር የሌለ በመሆኑ፣ በመንግሥት የፍትሕ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የሚታቀፉ አይደሉም፡፡[47]

ሸሪዓ ከዓለማዊ የሕግ ፍልስፍና በተለየ፣ ከአስገዳጅ *(ዋጂብ)* እና ክልከላ *(ሀራም)* የሕግ ቅርጾች በተጨማሪ፣ የተወደደ *(መንዱብ)*ና የተጠላ *(መክሩሕ)* የተሰኙ ሰፊውን የሸሪዓ ክፍል የሚሸፈኑ የሕግ ቅርፆች አሉት፡፡ እነዚህ የድንጋጌ ዓይነቶች በተበዳይ በቀረበ አቤቱታ መሠረት በፍርድ-ቤት ወይም በሌሎች የፍትሕ አካላት ሊፈጸሙ አይችሉም፡፡ ወይም በሕግ ቋንቋ ዳኝነት የሚጠየቅባቸው *(Justiciable)* አይደሉም፡፡ ስለሆነም፣ በዚህ ባህርያቸው የሸሪዓውን ሃይማኖታዊ ገጽታ በጉልህ የሚያሳዩ ናቸው፡፡[48] እዚህ ላይ ሊሠመርበት የሚገባው ነጥብ፣ አንድ ድንጋጌ በቀዳሚ የሸሪዓ ምንጮች ውስጥ *ሙባህ* (ፍቁድ) ወይም፣ *የመንዱብ* ወይም *መክሩሕ* ቅርጽ ቢሰጠውም፣ በመንግሥታዊ የሕዝብ አስተዳደር ማዕቀፍ ውስጥ ወቅታዊ ተጨባጭ እውነታዎችንና ሕዝባዊ ጥቅም ታሳቢዎችን *(Public Interest Considerations)* መሠረት በማድረግ *በኢጅቲሓድ* አማካይነት የአስገዳጅነት *(ዋጂብ)* ወይም ክልከላ *(ሀራም)* ቅርጽ ሊሰጠው የሚችል መሆኑ ነው፡፡[49]

ወደ ሸሪዓ የሕግነት *(Positivistic)* ባሕርይ ስንመጣ፣ በሰዎች የርስበርስ ግንኙነት ውስጥ ፍትሕ፣ መልካም ሥነ-ምግባርና ሞራል እንዲሰፍን ለማድረግ፣ ከሰላምና ጸጥታ አንጻር የግለሰቦችንና የማሕበረሰቡን ደህንነት ለማስጠበቅ፣ የሕዝቦችን ፖለቲካዊ፣ ማሕበረሰባዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማትና መሻሻልን እውን ለማድረግ በየዘርፉ የተቀረጹ ጠቅላላና ዝርዝር የሸሪዓ ድንጋጌዎች፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ በምድራዊ አኗኗር ላይ ለውጥ ወይም ተጽእኖ የሚያሳርፉ በመሆኑ፣ በፍትሕ አስተዳደርና ተቋማት አማካይነት አስገዳጅ የአፈጻጸም ሥርዓት ሊዘረጋላቸው ይቻላል፡፡[50] ግባቸውም ከላይ የተጠቀሱትን ምድራዊ ዓላማዎች በማሳካት፣ በግለሰብም ሆነ በማሕበረሰብ ደረጃ ቀላልና ምቹ ምድራዊ ሕይወት እውን ማድረግ *(መሷሊህ)* ነው፡፡[51] ይህ ሲባል ሕጎቹን መተላለፍ፣ በምድራዊ የፍትሕ አስተዳደር ሊያስከትለው ከሚችለው የሕግ ተጠያቂነት ውጪ ከሕልፈት በኋላ በአምላክ ፊት አያስጠይቅም ማለት እንዳልሆነ ይነዘቧል፡፡

## 3.2. ሸሪዓ እና አመክንዮ

ሃይማኖትን (እምነትን) እና ሕግን ለመረዳት የሚቻልበት ወሳኝ መሣሪያ አመክንዮ ነው፡፡ ሰው ምክንያታዊ ያልሆነን ሐሳብ መረዳት አይችልም፤ ቢሞክርም በቅን ልቦናው ሊቀበለውና ሊያምንበት አይችልም፡፡ ስለሆነም ኢስላም በእምነትም ሆነ በሕግ ገጽታዎቹ፣ የሰውን ምግባር መቅረጽ የሚችለው ምክንያታዊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ያለው የእምነትም ሆነ የሕግ አቀራረብ በውጤቱ ንፍቅናና ማስመሰልን የሚፈጥር እንጂ እውነተኛ የአስተሳሰብና የተግባር ውጤትን አያመጣም፡፡[52] አመክንዮ የሰው ግንዛቤ ቁልፍና ወሳኝ

---

[47] Muhammad Hashim Kamali, The Sharia: Law as the Way of God, Abdullah Ahmad Badawi (ed.), Islam Hadhari, A Model Approach for Develeopment and Progress, MPH Publishing, p. 164.
[48] Ibid.
[49] Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, *supra* note 4, p. 47.
[50] Ibid, pp. 46-47.
[51] Ibid, pp. 27-33.
[52] Muhammad Hashim Kamali, Methodological Issues in Islamic Jurisprudence, *Arab Law Quarterly*, Vol. 11, No. 1 (1996) p. 14.

መንገድ መሆኑን ቁርአን በበርካታ አንቀጾች በአንክሮ ይገልጻል፡፡[53] ስለዚህ በሸሪዓ እና በአመክንዮ መካከል ያለው ትስስር የተቃርኖ ሳይሆን፣ አመክንዮ ሸሪዓን መገንዘቢያ፣ ሸሪዓ ላይ መድረሻ ዘዴ ነው፡፡ የኢስላም የሕግ ማዕቀፍ ዘዴ በዋናነት ከመለኮታዊ ራዕዩ ይልቅ፣ በ*ዑለማእ* ግለሰባዊ-አመክንዮአዊ ምርምር የበለጸገ ከመሆኑ አኳያ፣ ‹የሊቃውንት ሕግ› የሚል መገለጫ የሚሰጠው ምክንያታዊ አስተሳሰብ ሸሪዓውን በመዘርጋት ረገድ ያለውን ከፍተኛ ድርሻ አጉልቶ ያሳያል፡፡ ከላይ አመክንዮ ሸሪዓን የምንረዳበት መሣሪያ ነው ሲባል፣ አንድ ልዩ ድንጋጌ የተደነገገበትን መንስኤ ምክንያትና *(ዒላሕ)* እና ዓላማ *(ሂክማሕ)* የሚለይበት መንገድ ነው ማለት ሲሆን፣ አመክንዮ ከሁለቱ የሸሪዓ ክፍሎች በ*ሙዓመላት* ሕጎች ላይ በተለየ ያለው ሚና እጅግ የጎላ ነው፡፡ የአምልኮ ሕግጋት *(ዒባዳት)* የተደነገጉበት ጠቅላላ ዓላማ፣ ሰው ለአምላኩ ያለውን ታዛዥነትና ተገዥነት ማሳያ መሆኑን መሠረት በማድረግ ጥቅል የድንጋጌ ምክንያት ማብራሪያ ማስቀመጥ ቢቻልም፣ እያንዳንዱ የአምልኮ ተግባራት በተናጠል ያላቸውን የድንጋጌ ምክንያትና ዓላማ ለመለየት የሚደረግ ምርምር ከግምትና መላምት ያልዘለለ ነው፡፡[54] በሌላ በኩል፣ የሰውን የእለት-ተዕለት እንቅስቃሴ የሚገዙ መለኮታዊ ሕጎች *(ሙዓመላት)* ተጨባጭ ምድራዊ ዓላማና ግብ ያዘሉ በመሆኑ፣ ሕግጋቱ የተደነገጉበት ምክንያት *(ዒላሕ)* እና ሊያሳኳቸው ያሰቧቸውን ዓላማዎች በአመከንዮአዊ ምርምር መለየት ይቻላል፡፡[55]

በአንዳንድ የቤተሰብ፣ የውርስ፣ የወንጀልና ሌሎች ጥቂት ጉዳዮች ላይ ያሉ ዝርዝር መለኮታዊ ድንጋጌዎች፣ ገዥነታቸው በጊዜና በቦታ ያልተገደበ እና (አከራካሪነቱ እንዳለ ሆኖ) የማይሻሩና የማይለወጡ ቢሆኑም፣ ከእነዚህ በጣት ከሚቆጠሩ ልዩ ድንጋጌዎች ውጪ፣ ሁሉም ሕግ-ነክ የቁርአን አንቀጾችና የ*ሀዲስ* ዘገባዎች፣ በልዩ ልዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ የሕግ መርሆዎችንና ለዝርዝር ድንጋጌዎች መንደርደሪያ የሆኑ ጥቅል መርሆዎችን የሚዘረጉ ናቸው፡፡[56] የ*ተዕሊል* ምርምር በአምልኳዊ ሕጎች ላይ አግባብነት የሌለው ቢሆንም፣ *በሙዓመላት* ሕጎች ላይ ግን የሚፈቀድ ብቻ ሳይሆን፣ የሚበረታታ፣ እንዲሁም በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ደግሞ አስገዳጅ ተግባር ሊሆን የሚችል ነው፡፡[57] እጅግ ሰፊውን ድርሻ የሚይዘውና የግለሰብና የማሕበረሰብ መስተጋብሮችን የሚገዛው የሸሪዓ ክፍል ግን በ*ዑለማእ* አማካይነት በአመክንዮአዊ እሳቤ *(ኢጅቲሓድ)* የተዘረጋ በመሆኑ የየወቅቱን ማሕበረሰብ ተጨባጭ እውነታ ግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊው ማሻሻያና ለውጥ ሊደረግበት የሚችል ነው፡፡

የትኛውም የሸሪዓ ዓለማዊ ሕግ ያለአንድ ምክንያት ወይም ዓላማ አልተደነገገም፡፡[58] እነዚህን የድንጋጌ ምክንያቶች በመመርመር *(ተዕሊል)* የሕጎችን አተረጓጎምና አፈጻጸም ለማቃናት፣ ብሎም በዓላማዎቹ ላይ በመንተራስ የሕግ ማሻሻያና ለውጥ የሚደረገው፣ ወይም ለአዲስ ሕጎች አቀራረጽ መንደርደሪያ የሚሆኑት፣ አመክንዮን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

[53] Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, *supra* note 4, p. 54.
[54] Ibid, p. 55.
[55] Ibid.
[56] Kamali, Source, Nature and Objectives of Shariah, *supra* note 1, pp. 219-220.
[57] Taha Jabir Alwani, The Crisis of Thought and *Ijtihad*, *American Journal of Islamic Social Sciences*, Vol. 10, No. 2, p. 236.
[58] አልዩ አባተ፣ የሸሪዓ ሕግ ዓላማዎች *(መቃሲድ አሽ-ሸሪዓሕ)፣ Bahir Dar University Journal of Law,* Vol. 7 No. 2, (2017), p. 271.

በተጨማሪም በቁርአን ውስጥ የመሻር *(ነስኽ/Abrogation*) ግንኙነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስናይ፣ የተሻሩ ድንጋጌዎች ከመነሻው የተደነገጉበት ምክንያት *(ዒላሕ)* በሌለበት ወይም ነባራዊው እውነታ በተለወጠበት፣ ገዥነታቸው ሳይቋረጥ በየትኛውም ሁኔታ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ቢደረግ ከምክንያታዊ አስተሳሰብ ጋር የሚጻረር በመሆኑ፣ በምትካቸው ለወቅቱና ለተጨባጭ ሁኔታው የተሻለና ተስማሚ በሆነ ድንጋጌ መተካቱ፣ ወይም በአጭር አነጋገር *ነስኽ* በቁርአን ውስጥ የመኖሩ ምስጢር፣ አመክንዮ ሸሪዓን በመረዳት እና በመዘርጋት ሂደት ላይ ቁልፍ ሚና ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ነው።[59]

## 3.3. ሂደታዊነት እና ነባራዊነት

በግለሰብ እና በሕብረተሰብ ላይ ለውጥን ለማምጣት ከሚውሉ ዓይነተኛ መሣሪያዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ሕግ ነው። ሌሎች ከሕግ ተርታ የሚሰለፉት ትምህርት (እውቀት)፣ ሃይማኖት እና ባህል ይገኙበታል። ሕግ የማህበረሰብን ወይም የሃገርን አኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖሊቲካዊ ገጽታ ወደ ተሻለ ለመምራት እና ለመቀየር ወሳኝ እና ቀዳሚ ሚናውን መጫወት የሚችለው የሕብረተሰቡን ነባራዊ ሁኔታ ተከትሎ ቀስ በቀስ አመለካከትና ምግባርን የሚያስተካክልበትን ሂደታዊ አካሄድ *(ተንጂም/Gradualness*) ሲከተል ነው። በእድገት ደረጃው ከፍ ያለ እና ከማሕበረሰብ ተጨባጭ እውነታ፣ የሥልጣኔ ደረጃ እና ልማድ በጣም የራቀ ሕግ በማሕበረሰቡ ላይ በመጫን ሕጉ የወጣበትን ዓላማ ማሳካት ፈጽሞ የማይታሰብና፣ ብዙውን ጊዜ ሕጉ እንዲመራው ከታሰበው ሕዝብ በኩል አሉታዊ አጸፋ ሲያጋጥመው ይስተዋላል። ስለዚህ ሕግ ያነገበውን ዓላማ ለማሳካት እና ሊያስርጸው የፈለገውን እሴት እውን ለማድረግ ከሕብረተሰቡ እውነታ እጅግም ሳይርቅ፣ በጣምም ሳይቀርብ የተጠናና የተመጠነ ርቀቱን ጠብቆ ደረጃ በደረጃ ሕብረተሰቡን ወደ ተሻለ የሚለውጥበትን ሂደት እንዲከተል ማድረግ ያስፈልጋል።

ከዚህ መርሆ አኳያ የሸሪዓን ባህርይ ስንመለከት፣ ቀዳሚ የሆኑት የቁርአን እና የሱናሕ ሕግጋት የወረዱበትን ታሪካዊ ዳራ ስንመረምር ሂደታዊ ሆኖ እናገኘዋለን። ቁርአን መውረድ ከጀመረበት ቅጽበት አንስቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ 23 ዓመታትን መፍጀቱ ለዚህ አብነት ነው።[60] ቁርአን መጀመሪያ በወረደባቸው የነቢይነት ዓመታት ላይ ሙሉ በሙሉ የሕብረተሰቡን እምነትን እና አመለካከትን በመቅረጽ ላይ ያተኮረ ነበር። ነቢዩ ሙሀመድ መካህ በነበሩባቸው 13 ዓመታት ሲወርዱ የነበሩት የቁርአን አንቀጾች አምላካዊ ጽንሰ-ሐሳብን፣ መልካም ሥነ-ምግባር እና ግብረ-ገባዊ እሴቶችን የሚያስተምሩ ነበሩ። ሕግ-ነክ መለኮታዊ ራዕዮች በዋናነት መውረድ የጀመሩት ከኢስላማዊው ሥደት *(ሒጅራ)* በኋላ በመዲና ከተማ አነስተኛ የሙስሊም ማሕበረሰብ መመስረቱን ተከትሎ ነው።[61] ከዚህ የምንገነዘበው፣ ቁርአን በአወራረዱ የሚያናግራቸውን ሕዝቦች ተጨባጭ ሁኔታ ተከትሎ፣ ሙስሊሞች መካህ በነበሩበት ጊዜያት አስገዳጅ የአምልኮም ሆነ የሙዓመላት ሕጎችን መደንገግ ነባራዊ እውነታው የማይፈቅድና ከተግባር ይልቅ በቅድሚያ እምነትንና አስተሳሰብን መቅረጽ አንገብጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ከዚያም በመዲና የሙስሊሞች ቆይታ፣ የነበረውን የእምነት

---

[59] Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, *supra* note 4, p. 55.

[60] Ibid.

[61] Yasir Qadhi, *Introduction to the Sciences of the Qura'n*, Al-Hidayah Publishing and Distribution, UK (1999), p. 86.

ጥንካሬ እና ሕብረተሰቡ ያሳየውን የሕግ ተገዥነት አቅም ታሳቢ በማድረግ፣ ልዩ ልዩ ግንኙነቶችን የሚገዙ ሕግጋት መውረድ ጀመሩ፡፡ መዳናዊው የሕግ አወራረድም በራሱ ሂደታዊ ነው፡፡[62] ሙስሊሞችን አስገዳጅ የሆኑ ትዕዛዛዊ ወይም ከልካይ የሆኑ ሕጎች የማሕበረሰቡን የለውጥ እርምጃ እና ዝግጁነት ተከትለው ደረጃ በደረጃ ሲወርዱና ልምምድ ወይም ሥልጠና በሚመስል መልክ ሲገለጹ የነበሩት መለኮታዊ ድንጋጌዎች፣ በሰው ልጅ ታሪክ ድንቅ የሆኑ ሰብዕናዎችን ማፍራት፣ እና ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ግብረ-ገባዊ ሚዛን የተጠበቀበት ሕብረተሰብ መፍጠር ችሏል፡፡

## 3.4. ተለማጭነት እና ቀጣይነት

በብዙኃኑ ዘንድ እንደሚነገረው፣ ሃይማኖታዊ ሕግ በተለይ የሸሪዓ ሕግ ከአምላክ የወረደ ስለሆነ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የማይቀየርና የማይለወጥ ነው፡፡ ስለሆነም ለሁኔታዎች መለወጥ እና ከተጨባጩ ጋር መጣጣም ለሚለው የሕግ ጽንሰ-ሐሳብ ተገዥ ያልሆነና ለየትኛውም ሕብረተሰባዊ ለውጥ ምላሽ የማይሰጥ ነው የሚል እሳቤ በሥፋት ይስተጋባል፡፡ ነገር ግን ይህ አመለካከት፣ ሸሪዓዊ መሠረት የሌለው ሲሆን፣ እንዲያውም ከዚህ አስተሳሰብ ፍጹም ተቃራኒ በሆነ መልኩ፣ ሸሪዓ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ማገናዘብ እና ለአዳዲስ ጉዳዮች ምላሽ መስጠት፣ የሕግ ማዕቀፉ አካል እና ዋነኛ መለያ ባሕርይው እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡[63] ሸሪዓ፣ *ኢጅቲሓድ* እና በስሩ ያሉ እንደ *ኢስቲሰላሕ* (የሕዝብ ጥቅም)፣ የሕግ አፈጻጸም አማራጭ (ርትዕ - *ኢስቲህሳን*)፣ ተመሳሳይ አመክንዮ *(ቂያስ)* እና ሌሎችም የሕግ ምርምር መርሆዎች፣ ከቁርአን እና *ሱናሕ*፣ ቀጥሎ በሦስተኛ ደረጃ የሕግ ምንጭ በመሆን የሚያገለግሉበት ዋነኛ ምክንያት፣ ሸሪዓ በምሁራዊ የሕግ አተረጓጎም አማካይነት ለተለዋዋጭ ሁኔታዎች ያለው አግባብነት ቀጣይ እንዲሆን፣ ማሻሻል እና መለወጥ እንዲቻል ለማድረግ ነው፤ የምርምር መነሻ ንድፈ-ሐሳቦቹም ይህን የቀጣይነት *(Continutity)* እና የተለዋዋጭነት *(Adaptability)* ባህርይ ማሳኪያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡[64] ይህ ባይሆን ኖሮ ግን የሸሪዓ ሕግጋት መጀመሪያ ለወረዱበት ልዩ ሁኔታ እና ምክንያት ብቻ አግባብነት እና ጠቀሜታ ይኖራቸውና ከዚያ በኋላ የጊዜ ሂደትን ተከትሎ ለመጣው ማህበረሳባዊ ለውጥ ምላሽ መስጠት ባልቻሉ ነበር፡፡ ነገር ግን በ*ኢጅቲሓድ* እና በ*መቃሲድ* መርሆዎች አማካይነት የሸሪዓ ሕግ በጊዜና በሕብረተባዊ እውነታዎች ሳይወሰን ዘመን እና ትውልድ ተሻግሮ ገዥነቱ እንዲቀጥል ይችል ዘንድ የተለዋዋጭነትና የቀጣይነት ባህርይው የተረጋገጠ ነው፡፡ በተለይ ቁርአናዊ የሕግ ድንጋጌዎች *(አያት አል-አህካም)* በዋናነት የጥቅልነት *(ዓም)* እና ያልተለየ *(ሙጥለቅ)* ባህርይ ያላቸው መሆኑና ለትርጉም ክፍት የተደረገበት መለኮታዊ ጥበብ የሸሪዓውን ቀጣይነት እና ተለማጭነት ለማረጋገጥ ነው፡፡

የሸሪዓ ዓላማዎችን *(መቃሲድ)* ማሳካት የሚቻለው እንደየሁኔታው የሚመጥን፣ በተጨባጭ ላጋጠሙ ተግዳሮቶች ችግር-ፈቺ የሆኑ ሕጎች ሲቀረጹ ነው፡፡ ሁኔታዎቹ ቢለዋወጡም ተፈጻሚ የሚደረገው ሕግ አንድ ዓይነት የሚሆን ከሆነ፣ የሕጉን ዓላማ እና መንፈስ ማሳካት አይቻልም፡፡ የሸሪዓ ሕግ ዓላማዎች በጠቅላላው ጥቂት የሚባሉ፣ ቋሚ እና

[62] Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, *supra* note 4, p. 59.

[63] Ibid, p. 49.

[64] Ibid.

የማይቀየሩ ቢሆኑም፣ እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ማድረስ የሚቻለው በየጊዜው እውነታውን ያገናዘቡ የተለያዩ ሕጎች ሲቀረጹ ነው፡፡

የሸሪዓ የተለዋዋጭነትና የቀጣይነት ባህርይ ጥቅል የሸሪዓ ዓላማዎችን እንደማይመለከት ሁሉ የ*ዒባዳት* ሕጎችንም አይመለከትም፡፡ የአምልኮ *ሥነ-ሥርዓት*ን የሚዘረጉ የቁርአን እና የ*ሱናሕ* ድንጋጌዎች በሁኔታዎች መለወጥ ምክንያት የማይለወጡ እና በማንኛውም ሁኔታ እንደጸኑ የሚቆዩ ናቸው፡፡[65] አምልኳዊ የሸሪዓ ድንጋጌዎች፣ ለምሳሌ ያህል የ*ሶላሕ*፣ የ*ፃም*፣ የ*ሐጅ* ወዘተ ሕግጋት የማይቀየሩ ናቸው፡፡ በ*ኢጅቲሓድ* ሊጨመር ወይም ሊቀነስ ወይም ሊሻሻል የሚችል የአምልኮ *ሥርዓት* የለም፡፡ ምንም እንኳ የቁርአን የ*ዒባዷሕ* ድንጋጌዎች በጣም ጥቂት ቢሆኑም፣ በነቢዩ የተግባር ማሳያዎች *(ሱናሕ)* ዝርዝር አፈፃፀማቸው ተብራርቷል፡፡[66] በተጨማሪም ልዩ እና ግልጽ የሆኑት፣ ጥቂት የ*ሙዓመላት* ሕጎች፣ ለምሳሌ ያህል በውርስ ሕግ ላይ ያሉት ድንጋጌዎች ዝርዝር እና ግልጽ ከመሆናቸው አኳያ ለትርጉም ያልተጋለጡ በመሆኑ ማሻሻያ ሊደረግባቸው አይችልም፡፡ ያም ሆኖ አብዛህኛው የፍትሐ-ብሔር፣ የንግድ፣ የወንጀል፣ የፖሊሲ እና አስተዳደር *(ሲያሳሕ አሹሽርዒያሕ)* እና ሌሎች ዘርፎች *ሥር* ላይ ያሉት ሕጎች ጥቅልና ለትርጉም *(ኢጅቲሓድ)* የተጋለጡ መሆናቸው፣ ተለማጭነት የሸሪዓ ዓይነተኛ መገለጫ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ ከጥቂት ጉዳዮች በስተቀር፣ ሁሉም ቁርአናዊ እና የ*ሱናሕ* ሕጎች የመርሆነት ባህርይ ያላቸው መሆኑ፣ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን መሠረት ያደረጉ ዝርዝር ሕጎች ለመቅረጽ፣ እና ከዚያም የሕግ ለውጦችና ማሻሻያዎችን ለማድረግ እንዲቻል ነው፡፡[67]

የሸሪዓ ሕጎች ለ*ኢጅቲሓድ* ካላቸው ተጋላጭነት አንጻር፣ ወይም በሌላ አነጋገር፣ በሁኔታዎች መለዋወጥ ታሳቢነት ሊሻሻሉ ወይም ሊለወጡ ከመቻላቸው አኳያ በሁለት ጥቅል ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ፡፡፤እነዚህም *ቀጥዒ* (ወሳኝ - *Definitive*) እና *ዞኒ* (አሻሚ - *Speculative*) ይሰኛሉ፡፡ *ቀጥዒ* ማለት በቋንቋዊ አገላለጻቸው ለትርጉም ያልተጋለጡ፣ ራሳቸውን ችለው መቆም የሚችሉ ወሳኝ ድንጋጌዎች ሲሆኑ፣ *ዞኒ* ማለት ደግሞ ቋንቋዊ አጠቃቀማቸው ለትርጉም የተጋለጠ፣ ወይም ቋንቋዊ ችግር ባይኖርባቸው እንኳ ተዓማኒነታቸው አጠያያቂ በመሆኑ፣ ራሳቸውን ችለው ደንጋጊ (ወሳኝ) መሆን የማይችሉ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡[68]

አንድ የሸሪዓ ድንጋጌ በሁለት መመዘኛዎች መነሻነት *ቀጥዒ* ወይም *ዞኒ* ምድብ *ሥር* ሊወድቅ ይችላል፡፡ አንደኛው፣ ከቋንቋዊ አገላለጽ አንጻር ቁርኣናዊ አንቀጹ ወይም የ*ሀዲሰ* ዘገባው ጥቅል (*General/ዓም*)፣ ወይም ያልተገደበ/ያልተለየ (*Absolute/ሙጥለቅ)*፣ ወይም አሻሚ *(ሙጅመል/Ambigious*) ከሆነ፣ ትርጉም የሚያስፈልገው በመሆኑ፣ ለ*ኢጅቲሓዳዊ* ትንታኔ እና ለተለያዩ ሐሳቦች እንዲሰነዘሩ በር የሚከፍት በመሆኑ፣ *ዞኒ* ድንጋጌ ይባላል፡፡ አብዛኛዎቹ የቁርአን ሕግ-ነክ አንቀጾች፣ ጥቅል መርሆዎችንና ለተለያዩ ትርጉሞች የተጋለጡ አሻሚ ድንጋጌዎችን ያዘሉ በመሆናቸው፣ በ*ዞኒ* ክፍል *ሥር* የሚመደቡ ናቸው፤

[65] Ibid, p. 50.
[66] Kamali, *Principles of Islamic Jurisprudence*, *supra* note 21, p. 31.
[67] Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, *supra* note 4, p. 50.
[68] Kamali, Source, Nature and Objectives of Shariah, *supra* note 1, p. 221.

በመሆኑም *ኢጅቲሓድ* ሊደረግባቸውና አስፈላጊው የሕግ ለውጥና ማሻሻያ ቢደረግባቸው የማይከለክሉ ናቸው፡፡[69]

ሁለተኛው *የቀጥዒ/ዞኒ* መወሰኛ መስፈርት፣ የምንጩ ተዓማኒነት ነው፡፡ ቁርአንን በተመለከተ የተዓማኒነት *(ሱቡት - Authenticity)* ጥያቄ ሊነሳበት የማይችል መሆኑ፣ በሁሉም ሊቃውንት ዘንድ የታመነና የተረጋገጠ በመሆኑ ቁርአን ከተዓማኒነት አኳያ *ዞኒ* ሊባል አይችልም፡፡[70] ነገር ግን ሁለተኛ የሸሪዓ ምንጭ የሆነዉ *ሱናሕ*፣ ከነቢዩ ሙሀመድ ሕልፈት ከአንድ ምዕተ-ዓመታት በኋላ በዘገባዎች *(አሃዲስ)* የተሰባሰበ እና የተጠናቀረ በመሆኑ፣[71] በአዘጋገቡ ሂደት ውስጥ በመስኩ ምሁራን በተለዩ እንከኖችና ድክመቶች *(ዒለል አል-ሀዲስ)* የተነሳ ሕግም ሆነ ሌላ ሐሳብ ያዘለ የ*ሀዲስ* ዘገባ ተዓማኒነቱ አጠያያቂ ሊሆን ስለሚችል፣ ሕግ-ነክ *ሀዲሶች (አሃዲስ አል-አህካም)* በዚህ መመዘኛ *ዞኒ* ክፍል *ሥር* ሊመደቡ ይችላሉ፤ በመሆኑም ለ*ኢጅቲሓድ* የተጋለጡ ይሆናሉ፡፡ ይህ ታሪካዊ እውነታ፣ በ*ሱናሕ* በኩል የተላለፈው የሸሪዓ ሕግ ለተለያዩ ሁኔታዎች ተለማጭ መሆን እንዲችል አድርጎታል፡፡[72] ከተዓማኒነት በተጨማሪ፣ የ*ሀዲሶች* ቋንቋዊ አወቃቀር፣ እንደ ቁርአናዊ ድንጋጌዎች ሁሉ ጥቅል *(ዐም)*፣ *ሙጥለቅ* (ያልተገደበ) ወዘተ. የድንጋጌ ቅርጾችን ሊይዙ የሚችሉ በመሆኑ፣ ይህ ቋንቋዊ ባህርያቸው የተለያየ ትርጉም እንዲሰጣቸው ምክንያት ስለሚሆን፣ በዚህ ረገድ *ዞኒ* እንዲሆኑና ሸሪዓው በ*ኢጅቲሓድ* አማካይነት የተለዋዋጭነት ባህርይ እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡[73]

ባጠቃላይ ቁርአን በጥቂት ጉዳዮች ላይ ልዩ እና ዝርዝር ሕግጋትን ያካተተ ቢሆንም በዋናነት ግን በሁሉም የኢስላም ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ማለት ይቻላል፣ ጠቅላይ የሕግ መርሆዎችን ብቻ በመዘርጋት በትርጉም አማካይነት ዝርዝር ሕጎችን የመቅረጹ *ሥራ* ለሕግ ምሁራን ተትቷል፡፡ ዝርዝር ሕግጋት የሚደነግጉት የቁርአን አንቀጾች ራሳቸው፣ በጥቅል መርሆዎች *ሥር* የሚካተቱ፣ ነገር ግን የመርሆዎቹን አተረጓጎም አቅጣጫ የሚያሳዩ የ*ኢጅቲሓድ* ማሳያዎች እንደሆኑ *ኢማም* አሹ-ሻጢቢ ያስረዳሉ፡፡[74] ይህን አይነተኛ የሸሪዓ ባህርይ *መሠረት* በማድረግ፣ በተለያየ ዘመናት እና ማሕበረሰቦች ውስጥ የነበሩ የሸሪዓ ሊቃውንት እንደ ወቅቱ እና አካባቢያዊ ሁኔታቸው፣ በ*ዞኒ* የቁርአን እና የ*ሱናሕ* ድንጋጌዎች ላይ የተለያየ አረዳድ እና አፈጻጸም ሲከተሉ ቆይተዋል፡፡

ሌላው የሸሪዓውን የተለማጭነት ባህርይ የሚያስረዳው ነጥብ፣ መጠነ-ሰፊ የሆነ የሕግ አረዳድ ልዩነት *(ኢኽቲላፍ)* እና በውጤቱም ራሳቸውን ችለው መቆም የቻሉ የሕግ ጥናት ክፍሎች *(መዛሒብ)* መፈጠራቸው በራሱ፣ ሸሪዓ የተለያዩ የሕግ አተረጓጎሞችን፣ አፈፃጸሞችን እና ብዝኃነትን የሚያስተናግድበት፣ ብሎም የሚያበረታታበት ሰፊ መደብ ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሸሪዓ ዋና ዓላማ የሕብረተሰቡን ጥቅም *(መሷሊሕ)* ማስጠበቅ፣ ጉዳትን ወይም ብልሹነትን *(መፍሰዳሕ)* መቀነስ/ማስወገድ እና ፍትሕን ማስፈን እንደመሆኑ፣ በውስጡ የያዛቸው ሕግጋት እነዚህን ታላላቅ ዓላማዎች ማሳካት

[69] Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, *supra* note 4, p. 50.
[70] Kamali, *Principles of Islamic Jurisprudence*, *supra* note 21, p. 21.
[71] Jamila Shaukat, Classifcation of Hadith Litrature, *Islamic Studies*, Vol. 24, No. 3 (1985), p. 1.
[72] Kamali, *Sharia Law: An Introduction*, *supra* note 4, p. 52.
[73] Ibid.
[74] Kamali, Source, Nature and Objectives of Shariah, *supra* note 1, p. 220.

በማይችሉበት ሁኔታ፣ እንዲያውም ደረቅ አፈፃፀማቸውን መከተል ያልተጠበቀ ግለሰባዊና ማህበረሰባዊ ጉዳትን፣ ከፍትሕ እና ከርትዕ ጋር የሚቃረን ውጤትን የሚያስከትል ከሆነ፣ ሕጎቹ አስፈላጊውን ማሻሻያ ብሎም ለውጥ ሊደረግባቸውና ዓላማዎቹ እውን መሆን የሚችሉበትን የሕግ አረዳድ እና ባህል ማስፈን ያስፈልጋል። ሸሪዓው በምንም አይነት ሁኔታ ቢሆን ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል አይችልም በማለት የሕጉን ቃላት ብቻ መከተል ያስፈልጋል የሚለው እይታ፣ ከግንዛቤ እጥረት መሆኑን እንደ ኢብን አል-ቀይም አል-ጀውዚያሕ እና ኢብን-ተይሚያሕ ያሉ የቀደምት ሊቃውንት፣ እንዲሁም እንደ ሙሀመድ ኢቅባል ያሉ የክፍለ-ዘመኑ የሙስሊም ተሃድሶ መሪዎች በአንክሮ ያስረዳሉ።[75]

## ማጠቃለያ

ስለሸሪዓ ሕግ ምንነት፣ መሠረተ-ሐሳቦችና መገለጫዎች የሚያጠና *ኡሱል አል-ፊቅሕ* የተሰኘ ጥንታዊ የእውቀት መስክ ያለ ሲሆን፣ በመስኩ የድርሳናት እድገት መሠረት፣ ሸሪዓ በኢስላም ሃይማኖት ውስጥ የሚገኝ መለኮታዊ የሕግ ማዕቀፍ ሲሆን፣ ሁለት መሠረታዊ ምንጮች አሉት፤ እነሱም፣ ራዕያዊ ምንጮች (ቁርአን እና *ሱናሕ)* እና አመክንዮኣዊ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* ናቸው። በራዕያዊ ቀዳሚ የሸሪዓ ምንጮች ውስጥ የሚገኙ ሕጎች በአብዛሀኛው የጥቅልነትና የመርሆነት ባህርይ ያላቸው በመሆኑ፣ ለአመክንዮአዊ የሕግ ምርምር መነሻ እና መንደርደሪያ የሚሆኑ እንጂ፣ ዘርፈ-ብዙና ተለዋዋጭ የሕይወት መስተጋብሮችንና ግንኙነቶችን የሚገዙ ዝርዝር ሕጎችን አይደነግጉም። በመሆኑም ሰፊው የሸሪዓ ሕግ ክፍል *(ፊቅሕ)* በኢጅቲሓድ አማካይነት እንዲዘረጋ ምክንያት ሆኗል።፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ ሸሪዓ፣ ‹የሊቃውንት ሕግ› የሚል መጠሪያ እንዳገኘ ተገልጿል። ሸሪዓ፣ በቀዳሚ ምንጮቹ ውስጥ በዋናነት የሕግ መርሆዎችን ብቻ ማካተቱ እና በጥቂት ጉዳዮች ላይ ብቻ ሲቀር፣ ጠቅላላው የሸሪዓ የሕግ ማዕቀፍ *ኢጅቲሓዳዊ ምንጭ* ያለው መሆኑ፣ ተጨባጭ እውነታዎችን የማገናዘብ፣ ሂደታዊ የለውጥ መንገድ የመከተል አቅም እና የተለማጭነት ባሕርያት እንዲኖሩት አስችሎታል።

በመጨረሻም በኢትዮጵያ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተፈጻሚ እየሆነ ያለው የቤተሰብ፣ የውርስ፣ የስጦታ *(ሒባ)* ወዘተ. የሸሪዓ ድንጋጌዎች፣ ከላይ በቀረበው የመግቢያ ዳሰሳ እና ከ*ኡሱል አል-ፊቅሕ* የጥናት መስክ ተቀንጭቦ እንደቀረበው፣ የሸሪዓ ጠቅላላ መርሆዎችን፣ ዓላማዎችን እና ባህርያትን መሠረት ያደረገና ያገናዘበ መሆን ይገባዋል።

[75] Ibid, p. 55.

# Sharia Law: Its Nature, Characteristics and Sources

*Alyu Abate Yimam*[*]

**Abstract**

Sharia can be defined as a divinely inspired legal system that exists within the religious of framework of Islam. Sharia represents two distinct but directly related sets of laws. The first segment consists of theories, principles, and objectives that serve as foundations for the promulgation and interpretation of specific laws. There is an independent discipline devoted to the study of philosophical and juristic principles of Sharia law known as Principles of Islamic Jurisprudence *(Usul al-Fiqh)*. The other part of Sharia is concerned with the regulation and guidance of every day interaction of individuals and society. This part of Sharia espouses detail legal rulings on the worldly matters *(Mua'malat)* on one hand and set of rules governing ritual matters *(Ibadat)* on the other. The *Mua'malat* laws have the objectives of realizing personal and public benefit, ensure peace and wellbeing and prevention of harm and corruption in a society. Sharia has all important attributes of rationality, gradualness and adaptability that are essential for effective governance of human relationships at all times and circumstances.

**Key Words**

Sharia*, Fiqh,* Source of Sharia, Quran, *Sunnah, Ijtihad*, Adaptability, Rationality

[*] (LL.B, LL.M, PhD Student, School of Law, Bahir Dar University) Email: alyuabate09@gmail.com